ሚያዚያ 2004 ዓ.ም.

# ወይ አማራ!

(ከአ.ይ.)

ያንን ያህል እንዳልተፈራ፣
የገኘ መደብ ተብሎ፣
በጅምላ እንዳልተጠራ፣
ይጠረግ ጀመር እንዳቧራ!?
እንደቆሻሻ እንደደንቃራ?
ቡና ለቃሚ በመሆን፣ ተቸግሮ ስለሠራ?
አማራው ዱሮ፣ ዱሮ፣ በሄደበት ተከብሮ፣
ከሕዝብ ጋር ተፈቃቅሮ፣
በክፉ በበጎው ተመካክሮ፣
ለጎረቤት ባህሉን አውሶ፣ ከጎረቤቱም ተበድሮ፣
በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ፣
በሄደበት ኑሮውን መሥርቶ፣
በእብሮነት ተጋብቶ፣
ዘር ሳይለይ ዘር ተክቶ፣
በኢትዮጵያ በሀገሩ፣
ወንጀል ሆነና መኖሩ፣
ይገፉ ጀምር፣ ይገፈተር፣
እንደመፃተኛ በመቆጠር?
የሂ የዘር ፖለቲካ፣ እንደሬት ነው የሚመር።
እነ ሽፈራው ሽጉጤ፣
ትከሻው ያበጠ ወጠጤ፣
ዘረኛው የደቡብ አጤ፣
ዘር ያጠፋ ጀመር በቀላጤ?
አሳዘነኝ መኖሬ፣ ይህን ለመስማት መቀመጤ።
የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳር እስከዳር፣
በአብሮነት አብሮ ሲኖር፣
እውን መሬት ጠቦት ነበር?
ሕዝብን ሕዘብ ጠልቶት ነበር?
ኧረ እግዚዖ ያንት ያለህ!
ምን እስክንሆን ታያለህ?
የአማራው ታሪክ ድሮም፣ ዛሬም፣
ኧረ እንደዚህ አልነበረም።
ጭፍን ፖለቲከኞች፣ ትናንት የተፈጠሩ፣
አማራውንና ኦርቶዶክሱን ለማጥፋት እያሤሩ፣
አብያተ-ክርስቲያናት ተደፈሩ፣
ገዳማት ተወረሩ፣
ዜጎች በዘር ተመነዘሩ፣
ነባር ክልሎች ተመዘበሩ፣
ታሪክ ጠፋ ያባት አደሩ።
ጌታ ሆይ! ፍርድህ ዘገየ፣ ረከሰ ሀገሩ።

EthioLion.Com

ይህንን መጻሕፍት ሲመሠክሩ፣
በምሕላ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ።
"...አጥሯን ለምን አፈረስህ?
መነገድ ሓላፊው ሁሉ ይቀጥፋታል።
የዱር ዕሪያ አረከሳት፤
የአገር አውሬም ተሠማራባት።
የሠራዊት አምላክ ሆይ!
እንግዴህስ ፊትህን መልስ፤
ከሰማይ ተመልከት፤ እይም።"
(መዝሙረ ዳዊት፦ 79 ቁ. 12-15)
አባይ ፀሐዬ የሚባል፣ ከፉ ዘረኛ ወያኔ፣
የቤተክርስቲያን አባቶችን ያሳደደ አረመኔ፣
ሁሉንም ላጋፍር የሚል፣ የመለስ ዜናዊ ምስለኔ፣
መነከሳቱንም ይዘልፋል? የሚኖሩትን በምናኔ?
ያ ደግሞ ጋሻጃግሬው፣ በታሪክ ድህነት የከሣ፣
"ዋልድባ ለአማራው ምኑ ነው?" አለና በድፍረት ተነሳ?
ጎንደሬ ፈረደብህ፤ ከቶ ምን ይሆን የአንተ አበሳ?
የተቸገረውን እየረዳህ እንዳልኖርክ ሁሉ ሳትሳሳ።
<u>ከለምፅ ሁሉ የከፋል፤ ይህ ዓይነት የታሪክ ጠባሳ፤</u>
ከባድ አውሎ ነፋስ ነው አቧራን የሚያስነሳ።
ወይ አማራ!
ሌላው ቢቀር በዲያስፖራ፣
ኧረ አንድ ሁንና ነብስ ዝራ፤
የተገፉትን ለመርዳት፣ በያለህበት ተጠራራ፤
እሰኪ ጣመኑ ይልቀቅህ፣ ብድግ በል ተንጠራራ።
ዛሬም እንደትናንቱ ያባቶችን ታሪክ ሥራ!
**<u>ራስህን ለማዳን</u>**፣ ፍፁም ይሉኝታን አትፍራ።
ለልጆችህ አታውርሳቸው፣ ውርደትና መከራ።
"የእሣት ልጅ አመድ" አትሁን፤ በማንነትህ ዛሬም ኩራ።
ያን ያህል **<u>አሥራት</u>** ተከፍሎ፣ ይህንን ያክል ኪሣራ?
የአማራው ወገናችን፣ የአማራው "ብሔረሰብ"፣
ምነው በአንድነት ቢሰባሰብ?
ይህ ዓይነት ግፍዕ ሲፈፀም፣
ፍርፋሪ መለቃቀም!?
በፍርሃት ውቅያኖስ ዓይን እያየ ዘቅጦ መስጠም?
ወይ አማራ!
ስንት ለሀገር እንዳልሠራ፣
ታሪኩ ይሁን መራራ?
እንደነ ኤሳው ታሪክ ብኩርናው ተሸጦ ለሽንብራ፣
አውራ ጣቱ በደም ለተነከረ፣ ለወያኔ ኩታራ።
(ዘፍጥረት፦ ም. 25 ቁ. 31-34)
ኧረ አንድ ሁን አማራ!
አቤት የዘመኑ መከራ!
መቼ ይሆን የሚያባራ?
ዛሬም ተነስ ተሰባሰብ፣ ጃሎ ብለህ አቅራራ፣
**<u>ባለፈው ብቻ አትኩራራ</u>**።

EthioLion.Com